Seattle Special Education PTSA®

## ወጤቶች ላይ መድረስ፦

# በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የልዩ ትምህርት መመሪያ

# የሲያትል ልዩ ትምህርት PTSA፡- አካታች ትምህርት ቤቶችን ለመደገፍ

## የእኛ ተልዕኮ፡-

የአካል ጉዳት ያለባቸው የተማሪዎች ቤተሰቦች በትምህርት ስርአት ውስጥ በሚሆኑበት ወቅት ድጋፍ እናደርግላቸዋለን።

የተሻሉ የትምህርት ግብአቶችን ለማምጣት እና ለሁሉም ተማሪዎች እድሎችን ለማመቻቸት በአጠቃላይ እና በልዩ የትምህርት ማህበረሰቦች መካከል ድልድይ እንገነባለን።

በልዩ የትምህርት ስርአት ውስጥ መሻሻሎችን ስንደግፍ ከወላጆች እና አስተማሪዎች ጋር አጋር በመሆን ነው።

## የምንሰራው፡-

### የምንደግፈው፡-

ለተማሪዎቻችን የተሻሉ ውጤቶችን ለማምጣት እና ተንከባካቢዎቻቸውን ለመደገፍ የሚሰሩ ኮሚቴዎችን ፈጥረናል።

### ኮሚቴዎች፡-

- የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ
- የህግ ድጋፍ
- አካታች ልምምዶች
- ገደቦች እና መገለል
- በጀት/ፋይናንስ
- የዘር እኩልነት እና አካታችነት
- ዲስሌክሲያ
- ውይይት
- አባልነት
- ገቢ ማሰባሰቢያ

### የወላጅ ትምህርት፡-

በወይበ መረብ የትምህርታዊ ጉባኤዎች ወይም የኦንላይን ስብሰባዎች ላይ ከባለሙያዎች እና ተሟጋቾች ልምድ ማካፈል ለመስማት እና ለማወቅ፤ የኛን ልጆች በተመለከተ የሚወጡ አዳዲስ ፖሊሲዎችን በተመለከተ በጋዜጣዎች፣ ማህበራዊ ሚዲያ፣ እና ሌሎች መንገዶች የሚወጡ መረጃዎች ማህበረሰቡን በጥሩ ተግባራት እና በወላጆች መብት ላይ ያላቸውን ለማሳወቅ፤ ወርሃዊ ስብሰባዎች ከተጋባዥ እንግዶች ጋር ማድረግ።

### መጠጣት እና መጨዋወት፡-

ቤተሰቦችን አንድ ላይ ለማገናኘት እና የአካል ጉዳተኞች ትምህርትን በምናሥሰበት ወቅት እርስ በእርስ እንዲደጋገፉ መደበኛ ያለሆነ መገናኘት እና ሰላምታዎች ይኖራሉ።


እውቂያ፡-
hello@seattlespecialeducationptsa.org
ልዩ ትምህርት PTSA
http://seattlespecialeducationptsa.org
https://www.facebook.com/SeattleSpecialEducationPTSA/
https://www.linkedin.com/company/seattle-special-ed-ptsa/
https://twitter.com/SeattleSEPTSA

Seattle Special Education PTSA

# ዋና 10 ጠቃሚ ምክሮች፡-

## የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች በማሰስ ላይ የሚረዱጠቃሚ ምክሮች ዝርዝር

1. **ይመዝግቡ**: የተማሪዎን IEP በተመለከተ የቀረበ ለውጥ ካለ የቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይጠይቁ (PWN)።

2. **ይከታተሉ፡-** የውይይት ነጥቦችን ለመያዝ እና የተደረጉ ውሳኔዎችን ለማወቅ፣ ማንኛውንምውይይቶች፣ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ውይይቶች ላይ፣ በኢሜይል ይከታተሉ።

3. **ጓደኛዎን ያምጡ፡-** በየ IEP ስብሰባዎች ላይ ማተኮር እንዲችሉ ይረዳዎ ዘንድ ማስታወሻ መያዣ ይዘው ይምጡ ። የግል አገልግሎት አቅራቢዎችን ለማምጣት መጠየቅም ይችላሉ።

4. **ውሂቡንን ይገምግሙ፡-** ቡድኑ ውሳኔ ሲያመጣ፣ ማጠቃለያዎችን ከመወሰን በፊት ቡድኑን ከቡድን ጋር ውሂቡንን እንዲያዩት እና እንዲከልሱት ይጠይቁ።

5. **መብቶችዎንን ይወቁ፡-** ያንብቡ እና ሁልጊዜም የወላጅን እና የተማሪን መብቶችን የሚያብራራውን ቅደም ተከተላዊ መመሪያዎችን ይመልከቱ፡

6. **ዝግጁ ሆነው ይቆዩ፡-** ሁሉንም የእርስዎን የተማሪ የ IEP/504 መዝገቦች ለማስገባት እና ለማቀናጀት ዝግጁ ስርአት ይፍጠሩ እና በስብሰባዎች ላይ ይዘዋቸው ይምጡ። የስራ ናሙናዎች ያካትቱ።

7. **ሃላፊነቱን የሚወስደው ማነው?** ልዩ ተግባር ሲያስፈልግ፣ የትኛው ሰው ተግባሩን እንድሚያከናውን እና መቼ እንደሚያከናውን እርግጠኛ ይሁኑ።

8. **የተማሪዎን ሁኔታ እንደ ራስዎ ጉዳይ ይውሰዱ፡-** በአመቱ መጀመሪያ ከየተማሪዎ አስተማሪ ጋር አጭር እና መደበኛ ያልሆነ ስብሰባ ያዘጋጁ እና የተማሪዎን የትውውቅ ቅጂ እና ከእነርሱ IEP/504 ጋር አብረው ይስጧቸው። ይህ በእቅዱ ውስጥ ምን እንደሚያስፈልግ እና ልጅዎን ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ እንደሚሆኑ ያረጋግጣል።

9. **ይመልከቱ፡-** የትምህርት ቤት ውስጥ ምልከታዎች ከግላዊ አገልግሎት አቅራቢዎች በተጨማሪ በወላጅ ወይም በተንከባካቢ መጠየቅ ይችላል። ጥያቄ በጽሁፍ መልኩ እና ቀደም ተብሎ መደረግ አለበት። በግምገማዎች ወቅት የዲስትሪክት ሰራተኞች ይገኛሉ።

10. **ይወያዩ፡-** የመወያያ መድረኩን ክፍት ያድርጉት እና በእርስዎ እና በየትምህርት ቤት ቡድን መካከል መተባበር እንዲኖር ያድርጉ። አንዳንዶች የመወያያ እቅድ መፍጠር እና ወደ IEP/504. ላይ መጨመር የሚረዳ ሆኖ አግኝተውታል። ውይይት(ሰነዶች እና ስብሰባዎች) በእርስዎ ቋንቋ መቅረብ አለባቸው።

- ይህ ሂደት የተዘጋጀበት ሁኔታ ቤተሰቦች ለመመልከት ከባድ ሊሆን እንድሚችል እንገምታለን፣ ስለዚህ እባክዎ ማንኛውንም እርዳታ ወይም ድጋፍ ከፈለጉ በገጽ 18 ላይ የቀረቡት ድርጅቶችን ያግኙ።

# የሰራተኛ ድርጅት ቻርት፡-

የልጁ ቡድን አባል ማን ነው እና የስራ ሃላፊነታቸው ምንድን ነው? ለቀላል ማዛመድ ይህንን ቻርት ከትምህርት ቤት ሰራተኛ እርዳታ በማግኘት ይሙሉት።

ተማሪ

## የግንባታ ደረጃ

- የስራ ቴራፒስት *
- አካላዊ ቴራፒስት *
- የንግግር ቋንቋ ፓቶሎጂስት *
- የትምህርት ቤት የስነልቦና ባለሙያ
- የተዛማጅ አገልግሎቶች ተቆጣጣሪ *
- የልዩ ትምህርት አስተማሪ
- የጉዳይ አስተዳዳሪ *
- ረዳትርዕሰ መምህር
- ርዕሰ መምህር
- የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪ/ዎች

## የዲስትሪክት ደረጃ

- የትምህርት ቤቶች ዳይሬክተር *
- የተማሪ አገልግሎቶች መሪ
- የፕሮግራም ልዩ ባለሙያ *
- የክልል ተቆጣጣሪ *
- የልዩ ትምህርት አስተዳዳሪ
- የልዩ ትምህርት ዋና ዳይሬክተር

*** የተዛማጅ አገልግሎቶች ተቆጣጣሪ**
የሁሉም ተዛማጅ አገልግሎቶች ተቆጣጣሪ (OT፣PT፣SLP)

*** የጉዳይ አስተዳዳሪ**
IEPን ይቆጣጠራል

*** የፕሮግራም ልዩ ባለሙያ**
በIEP ሂደት የማማከር እና ማሰልጠን አገልግሎት ላይ የትምህርት ቤቱን ቡድን ማገዝ

*** የክልል ተቆጣጣሪ**
የትምህርት ቤቱን ቡድን ይከታተላል እና የትምህርት ቤቱን የትግበራዎች ህግ መከተል ልምምዶችን ይቆጣጠራል።

*** የትምህርት ቤቶች ዳይሬክተር**
የትምህርት ቤቱን ርዕሰ መምህራን ይቆጣጠራል

SPS ልዩ ትምህርትመምሪያ፡-ስልክ- 206-252-0052
ኢሜይል፡- specialed@seattleschools.org
የልጆችን ማግኛ፣ አገልግሎቶች ከ3-5 አመት፣, 206-252-0805

# የቋንቋ አገልግሎት ማግኘት እና የተንከባካቢ መኖሪያ ሁኔታዎች

## ትምህርት ቤቶች ሙሉ የወላጅ እና ተማሪ ተሳትፎን መፍቀድ አለባቸው

### ለየIEP መሳሪያዎች በየኔ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ካልተሰጡ ምን ማድረግ አለብኝ?

ዲስትሪክቱ መሳሪያዎቹን በየእርስዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲያቀረብ ህጉ ይደነግጋል። ከየ IEP ስብሰባ ቀድሞ ለጉዳይ አስተዳዳሪዎ የመማሪያ መሳሪያዎችን በየእርስዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲያቀርብሎት የጽሁፍ መጠየቂያ ያስገቡ። በዚህ ጥያቄ ውስጥ ርዕሰ መምህሩን ያካቱት። ሰነዶች በየእርስዎ ቋንቋ ካልቀረቡ፣ ስብሰባውን ለመሳተፍ ግዴታ የለቦትም እና ሰነዶቹ በየእርስዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲቀርብ ስብሰባውን ለዚያ ጊዜ ማስተላለፍ ይችላሉ።
**ስጋቶችዎንበጽሁፍ ያስቀምጡ እና የክልል ተቆጣጣሪውን ለድጋፍ ያነጋግሩ።**

### የIEP መማሪያ መሳሪያዎች በትክክል ካልተተረጎሙ እና ምንም ፍቺ የሌላቸው ከሆኑ ምን ማድረግ አለብኝ?

ወላጆች እና አሳዳጊዎች ለተማሪዎቹ የልዩ ትምህርት ቁጥጥር እና ክትትል እና የእርስዎን ፍቃድ በሚያስፈልግባቸው ቦታዎች ላይ በየአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሙሉ ለሙሉ መረጃ እንዲሰጣቸው ህግ ይደነግጋል።

### በየIEP ሂደት ውስጥ የተማሪዬ የቋንቋ ፍላጎት የሚታየው እንዴት ነው?

የቋንቋ መዳረሻ በየIEP ዝግጅት ወቅት በውይይቱ ውስጥ የሚታሰብ እና አስፈላጊ ከሆኑት ልዩ ሁኔታዎች አንዱ ነው።

### በየIEP ስብሰባ ላይ ሙሉ ለሙሉ ለመሳተፍ የአስተርጓሚ ከፈለግኩ ምን ማድረግ አለብኝ?

የዲስትሪክቱ የትርጉም አቅራቢዎችን ወይም አስተርጓሚዎችን ያለ እርስዎ ወጪ ማቅረብ እንዳለበት ህጉ ይደነግጋል። ከየIEP ስብሰባ ቀደም ብሎ ለትርጉም እና የማስተርጎም አገልግሎት የጽሁፍ ጥያቄዎን ያስገቡ።

### ተማሪዬ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ መፈተን እና መገምገም ይኖርበታል?

አይ፣ ሁሉም ፈተናዎች እና መገምገሚያዎች ASLን ጨምሮ በየተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ መዘጋጀት አለባቸው።

### ለቋንቋ ድጋፍ ማንን ነው ማናገር ያለብኝ?

የእርስዎን የትምህርት ቤት ርዕሰ መስተዳደር እና የጉዳይ አስተዳዳሪን ያነጋግሩ። ለASL ትርጉም፣ የ504 አስተባባሪን በ **504coordinator@seattleschools.org** ላይ ያግኙ

### እንደ ተንከባካቢ የመኖሪያ አገልግሎት ከፈለኩ ምን ማድረግ አለብኝ?

የ ADA II አርዕስት "በክልሉእና የሃገሩ መንግስት ለህዝቡ በቀረበው መሰረት፣ ለሁሉም አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች፣ እና ተግባራቶች በአካል ጉዳት ላይ መሰረት ያደረገ ማግለልን ይከላከላል።" እንደ ተንከባካቢ ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ የሚረዱዎትን ማናቸውንም የመኖሪያ አገልግሎቶች ለሰራተኞች አስቀድመው ማሳወቅዎን ያረጋግጡ። አንዳንድ የመኖሪያ አገልግሎቶች ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡- በርቀት የሚደረጉ ስብሰባዎች፣ የASL ማስተርጎም፣ በኤሌክትሮኒክ ሊፈለግ በሚችል ጽሑፍ ቅርጸት የቀረቡ ሰነዶች፣ ዝግ መግለጫ ፅሁፎች፣ ሰነዶችን አስቀድሞ ለመገምገም የተራዘመ ጊዜ፣ ውሳኔዎችን ለመገምገም እና ምላሽ ለመስጠት የተራዘመ ጊዜ፣ ውይይትን ለመደገፍ የቀረቡ የእይታ መርጃዎች፣ ለስብሰባ ግልባጭ ፈጣን መዳረሻ፣ በግልፅ ቋንቋ የተፃፉ ሰነዶች እና የተቀዱ ስብሰባዎች።

# የድጋፍ ጠቃሚ ምክሮች

## መናገር በጣም ይበረታታል

ለአስተማሪዎች እና ለአስተዳዳሪዎች ጥያቄዎችን መጠየቅ ተገቢ አይደለም ተብሎ አይታሰብም። ስለ ተማሪዎ ትምህርት ያልዎትን ስጋት ለአስተማሪዎችና ለትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ለመናገር አይፍሩ። ስጋቶችዎን ለመግለጽ ሊረዱዎት የሚችሉ የውጭ ድርጅቶችን ያግኙ። አብዛኛዎቹ እነዚህ ድርጅቶች ድጋፍ እና አገልግሎት የሚሰጡት በተለያዩ ቋንቋዎች ነው። ስርዓቱን ለማሰስ እንዲረዳዎ ከሌሎች ወላጆች ጋር ግንኙነቶችን ይገንቡ።

አስፈላጊ ከሆነ ትምህርት ቤቶችን የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን የመጠየቅ መብት እንዳለዎት ያስታውሱ። ቋንቋውን የሚናገሩ ቢሆኑ እንኳ፣ የልጅዎን ጥንካሬዎች እና ተግዳሮቶች ለማስረዳት እንዲሁም በትምህርት ቤቱ ቡድን የሚነገረውን እና የእነዚያ ውሳኔዎች ውጤቶቹ ምን እንደሆኑ ለመረዳት እንዲረዳዎ አስተርጓሚ መጠየቅ ይችላሉ።

“አልገባኝም”፣ “ይህን መድገም ይችላሉ?”፣ “ምሳሌ ሊሰጡኝ ይችላሉ?”፣ “ተማሪዎችን ስለ ባህሌ እና ስለ አካል ጉዳተኝነት ምን እያስተማራችሁ ነው?” ማለት ምንም ችግር የለውም። በልጅዎ ክፍል እና ትምህርት ቤት ውስጥ እየተነገረ ያለውን እና ምን እየተከሰተ እንዳለ መረዳትዎ አስፈላጊ ነው። የሚነገረውን እና የሚወሰነውን ለመረዳት እና ስለ ተማሪዎ ጥንካሬዎች እና አካለ ጉዳተኛ መሆናቸው በትምህርታቸው ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድር ለማጋራት፣ እንግሊዝኛ ቢናገሩም እንኳ ለበለጠ ግልጽ እንዲሆን አስተርጓሚ ይጠይቁ።

የእርስዎን ባህል፣ እሴቶች እና ወጎች ከልጅዎ ክፍል እና ትምህርት ቤት ጋር መጋራት እርስ በርስ መግባባትን እና መከባበርን ለመጨመር ይረዳል።

የIEP ስብሰባዎች በጣም የሚያጨናንቁ እና ግራ የሚያጋቡ ሊሆኑ ይችላሉ። ጓደኛ ወይም ጠበቃ (አንዳንድ ድርጅቶች ይህንን ድጋፍ ይሰጣሉ) ማምጣት እርስዎ እና ልጅዎ የሚፈልጉትን ድጋፍ እያገኙ መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል።

በአስተማሪዎች እና በወላጆች መካከል አጋርነት መፍጠር ለተማሪዎ እድገት እና ስኬት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። በማንኛውም ጊዜ ከተማሪዎን አስተማሪዎች ጋር ለመገናኘት መጠየቅ ይችላሉ፣ እና ከጠየቁበዙዎች በኢሜይል ወይም በጽሁፍ ከእርስዎ ጋር ይገናኛሉ። በዓመቱ መጀመሪያ ላይ፣ ከእርስዎ ጋር የግንኙነት እቅድ ስለመፍጠር ከተማሪዎ አስተማሪ ጋር ይነጋገሩ እና እንደ አስፈላጊነቱ በየዓመቱ እቅዱን እንዲያስተካክሉ ይጠይቁ።

Seattle Special Education PTSA

# የመንገድ ካርታ፡-

**ተማሪዎ በትምህርት ቤት ውስጥ ተግዳሮቶች እያጋጠሟቸው ነው ነገር ግን የIEP ወይም የ504 እቅድ የላቸውም።**

1. በIEP እና 504 መካከል ስላለው ልዩነት ይማሩ፣ ገጽ 9ን ይመልከቱ።
2. ተማሪዎ በትምህርት ቤት የሚያጋጥማቸውን ማንኛውንም ችግር ይመዝግቡ።
3. ከስጋቶችዎን እና ጥያቄዎችዎን ለመምህሩ እና ለርእሰመምህሩ ያግለጹ። በሚመርጡት ቋንቋ፣ በጽሑፍ ያስቀምጧቸው።
4. የእርስዎን ስጋት እና ተማሪዎን ለመደገፍ ስላሉት አማራጮች ለመወያየት ከልጅዎ መምህር ጋር ስብሰባ ያቅዱ። ከስብሰባው በፊት አስተርጓሚ ይጠይቁ።
5. የስብሰባውን ማናቸውንም ውሳኔዎች እና የተደረጉትን ውይይቶች ይመዝግቡ እና ለአስተማሪው እና ርእስ መምህሩ በኢሜይል ይላኩ።
6. ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ሪፈራል እንዲጀመር፣ ለርእሰመምህሩ በጽሁፍ ያቅርቡ።
   https://www.parentcenterhub.org/evaluation-2/#model
7. ተማሪውን ለመመዘን ወይም ላለመመዘን የአውራጃውን ውሳኔ ይገምግሙ። ይህ በጽሁፍ ለእርስዎ መቅረብ እና ውሳኔያቸው መገለጽ አለበት፣ ለመመዘን ፈቃደኛ አለመሆንን ጨምሮ።
8. የምዘናውን ውጤት ለመገምገም እና ለ504 ወይም IEP ብቁነትን ለመወሰን ከIEP ቡድን ጋር የሚደረገው የግምገማ ስብሰባ ላይ ይሳተፉ።
9. ከምዘና ስብሰባው በኋላ በIEP ስብሰባ ላይ ይገኙ። ይህ በቀጥታ ከምዘና ስብሰባ በኋላ ወይም በቀጣይ ቀን ላይ ሊከሰት ይችላል። የIEP ቡድን የፕሮግራም አገልግሎቶችን መጠን እና በIEP ስብሰባ ላይ ያለውን ምደባ ይወስናል።
10. በዚህ ሂደት ውስጥ ጊዜዎን ይውሰዱ እና ማንኛውንም እና ሁሉንም ጥያቄዎች ይጠይቁ። ተጨማሪ ጊዜ ከፈለጉ፣ ስጋቶችዎን ለመፍታት ሌላ የIEP ስብሰባ ይጠይቁ።
11. ማስታወሻዎችዎን ለትምህርት ቤቱ ቡድን በመላክ እና በIEP ስብሰባ ወቅት የተደረጉ ውሳኔዎችን በሰነድ ለማስቀመጥ የሚያስችለውን PWN በመጠየቅ የIEP ስብሰባውን ይከታተሉ።
12. በIEP ግቦች ላይ ያለ መሻሻል ክትትል ሊደረግበት እና ለወላጆች ሪፖርት ሊደረግ ይገባል። የመሻሻል ሪፖርትን መጠየቅዎን እና የተማሪዎን መሻሻል በየሦስት ወር መገምገምዎን ያረጋግጡ።

# አስፈላጊ ቀናት እና የጊዜ ሰሌዳዎች፡-

በልዩ ትምህርት **IEP/504** ሂደት ውስጥ ሰዓቱ መቁጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

| አካሄድ | ምላሽ መስጫ ቀናት | |
|---|---|---|
| ለመመዘን ይወስኑ፡- | 25 የትምህርት ቀናት | **ምዘናዎች፡-** ለምዘና ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት 25 የትምህርት ቀናት። |
| ይመዝኑ፡- | 35 የትምህርት ቀናት | |
| ከምዘና በኋላ የIEP ስብሰባ ያካሂዱ፡- | 30 ቀናት | **IEP፡-** አንዴ ዲስትሪክቱ ተማሪው ብቁ መሆኑን ከወሰነ፣ IEP በ30 ቀናት ውስጥ መዘጋጀት አለበት። |
| ገለልተኛ የትምህርት ምዘና፡- | 15 ቀናት | **ገለልተኛ የትምህርት ምዘና፡-** IEE በወላጅ አማካኝነት በህዝብ ወጪ እንዲደረግ ከተጠየቀ፣ ዲስትሪክቱ በ15 ቀናት ውስጥ ተገቢውን ክፍያ በመክፈል ወይም በህዝብ ወጪ IEE እንዲደረግ በመስማማት ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል። |
| የIEP ግምገማ፡- | 12 ወራት | **የIEP ግምገማ፡-** የግለሰብ ትምህርት ፕሮግራሞች በየ12 ወሩ መከለስ አለባቸው። |
| ድጋሚ ምዘናዎች፡- | 3 ዓመታት | **ድጋሚ ምዘናዎች፡-** የIEP ድጋሚ ምዘናዎች በየ3 ዓመቱ ፣ እና በወላጅ ወይም በዲስትሪክቱ ሲጠየቁ ደግሞ በዓመት እስከ አንድ ጊዜ መከናወን አለባቸው። |
| ቅሬታዎች፡- | 1 አመት | **ቅሬታዎች፡-** የልዩ ትምህርት ማህበረሰብ ቅሬታዎች በህዝብ መመሪያ የበላይ ተቆጣጣሪ ጽህፈት ቤት (OSPI) መቅረብ እና መቀበል አለባቸው። OSPI በ60 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት። |
| ሂደት፡- | 2 ዓመታት | **የግለሰብ ህጋዊ መብት በግዛቱ መከበር፡-** ተገቢው ሂደት በበOSPI መቅረብ እና መቀበል አለበት። አንዴ ከቀረበ፣ ሁለቱም ወገኖች ያንን መብት ካላስቀሩት በስተቀር ድረስ፣ ትምህርት ቤቱ በ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ከወላጆች/ተንከባካቢዎች ጋር የመፍትሄ ሂደት ማካሄድ አለበት። የመፍትሔ ስምምነት ላይ ለመድረስ የ30 ቀን ጊዜ አለ። ስምምነት ላይ መድረስ ካልተቻለ፣ የግዛቱ የትምህርት መምሪያ ችሎት ለማሰማት እና ውሳኔ ለመስጠት 45 ቀናት አሉት። |

Seattle Special Education PTSA

# ትርጓሜዎች፡-

በልዩ ትምህርት IEP/504 ሂደት ውስጥ ያሉትን ቃላት እና አህጽሮተ ቃላት ትርጉም መስጠት

### የግለሰብ ትምህርት ፕሮግራም (IEP)፡-

ልጅዎ በህጋዊ መንገድ ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎቶች፣ መስተንግዶዎች እና ማሻሻያዎችን የሚገልጽ ሰነድ።

### ገዳቢነቱ ዝቅተኛ የሆነ አካበቢ(LRE)፡-

በሚቻለው መጠን ተማሪዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቻቸው ጋር ትምህርት መማር ይችሉ ዘንድ የሚያስገድድ የ IDEA መስፈርት መርህ እንጂ ቦታ አይደለም።

### ቅድሚያ የተጻፈ ማሳወቂያ (PWN)፡-

የልጅዎን የትምህርት ፕሮግራም በሚመለከት የተወሰኑ ውሳኔዎች ማሳወቂያ እና ማጠቃለያ **ከመተግበሩ በፊት** ለወላጆች ቀርቧል። ውሳኔ እና ለውጥ በተደረገ ቁጥር እና የተጠቆመ ሀሳብ ውድቅ በሚደረግበት ጊዜ ለወላጆች መቅረብ አለበት።

### ገለልተኛ የትምህርት ግምገማ (IEE)፡-

በልጅዎ የትምህርት ዲስትሪክት ባልተቀጠረ ባለሞያ በሆነ ፈታኝ የሚሰጥ ግምገማ። ወላጅ ወይም ህጋዊ አሳዳጊ በዲስትሪክቱ በተደረገው ግምገማ የማይስማሙ ከሆነ ይህንን መጠየቅ ይችላሉ።

### የተራዘመ የትምህርት አመት (ESY)፡-

ይህ በትምህርት እረፍት ጊዜዎች (የበጋ፣ የክረምት እረፍት, etc.) የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን የትምህረት ወይም ባህሪ ክህሎታቸውን ማሳደግ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የተነደፈ ነው። ብቁነት የሚወሰነው የሪግሬሽን ሰነድ እና ሪኩፐመንት እንዲሁም የተማሪውን አካል ጉዳት፣ እያደገ ያለ ክህሎት እና የእድገት ፍጥነት በሚመለከት ከIEP ቡድን በሚገኝ አስተያየት ነው

### ተግባራዊ የባህሪ ግምገማ (FBA)፡-

የአንድን ተማሪ ባህሪ ተግባር እና አዎንታዊ የጣልቃገብነት ድጋፍን ለመስራት የሚሆን የግምገማ መሳሪያ ነው።

### የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ (BIP)፡-

FBAን ተከትሎ አዎንታዊ የባህሪ ጣልቃገብነን እና የታለመውን ባህሪ ለመቀነስ የሚሆን ስልት እና የመተኪያ ባህሪዎች የሚደግፍ እቅድ።

### ነጻ እና ትክክለኛ የመንግስት ትምህርት (FAPE)፡-

FAPE ሁለት ትርጉሞች አሉት፤ ሁለቱም IEP ላለው ተማሪ የሚሆኑ ናቸው። ክፍል 504 አካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች እካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቻቸው ጋር ለአንድ አይነት ትምህርት ተደራሽ መሆን አለባቸው ይላል። በ IDEA መሰረት፣ FAPE ለአንድ ተማሪ ልዩ የሆነ ፍላጎት ግላዊ የተደረገ የትምህርት እቅድ ፕሮግራም እና ከዚያ ደግሞ ተማሪዎች የትምህርት ጥቅምን የሚያገኙበትን ይፈልጋል።

### ሂደት፡

ከትምህርት ቤት ጋር ስለልጅዎ ትምህርት ግጭቶችን የሚፈቱነት መደበኛ መንገድ። ለሂደት ማመልከት የሚችሉት ለልዩ የትምህርት ግጭቶች ብቻ ነው። ገለልተኛ የሆነ የችሎት መኮንን የማግኘት እና በሂደት ችሎቱ ላይ ማስረጃ እና ምስክር የማቅረብ መብት አለዎት።

Seattle Special Education PTSA

# የተማሪ ማስተዋወቂያ

## መደበኛ ያልሆነ ተማሪዎን ከትምህርት ቡደኑ ጋር የሚያስተዋውቁበት መንገድ

የተማሪ ማስተዋወቂያ ጠቃሚ የሆነ ነገር ግን በትምህርት ቡድኑ ግዴታ የማይፈለግ እርስዎ እና የእርስዎ ተማሪ ስለተማሪው ጥንካሬ እና ግብ ለመጪው አመት መረጃዎችን መስጠት የሚችሉበት ድጋፍ የሚያደርግ መሳሪያ ነው። ይህም በ ደብዳቤ፣ ሲቪ ወይም ፖስተር ያሉ መንገዶች ሊቀርብ ይችላል። ተማሪዎ በዚህ ወሳኝ የሆነ ደረጃ ላይ እንዲሳተፍ ያደርጉ።

### ሊካተቱ የሚችሉ ርእሶች የተማሪውን የሚከተሉ ጎኖች ያካትታል፤

- ጥንካሬዎች
- ውጤታማ የሆኑ ስልቶች
- የጤና ወይም የደህንነት አሳሳቢ ጉዳዮች
- ተግዳሮቶች
- ፍላጎቶች
- ግቦች
- ቋንቋዎች/ተግባቦት
- ባህላዊ ዳራ
- በቤት ውስጥ ያለ ባህል

### የተማሪ ማስተዋወቂያ ምሳሌ እነሆ




ለተማሪዎች የሚታተም ገጽ ያቅርቡ። ▶

# ስም

ክፍል

ጥንቃሬዎች

ባህላዊ ዳራ

የተረጋገጡ ጥንቃሬዎች

አሁን እየሰራሁበት ያለ ነገር

ጤና እና ደህንነት

ግቦች

ፍላጎቶች

በቤት ውስጥ ያለ ባህል

ቋንቋዎች

Seattle Special Education PTSA

# መፍጠን ያለባቸው ደረጃዎች፡

## ተማሪዎች የሚያስፈልገውን ድጋፍ እያገኙ አይደለም? ቀድሞ በ IEP/504 ለተለዩ ተማሪዎች መውሰድ የሚያስፈልጉ ደረጃዎች እነሆ

**1** በትምህርት ቤት ምክንያት ልጅዎ በትምህርት ቤትም ሆነ በቤት ውስጥ እያጋጠሙት ያለ ተግዳሮቶችን በሰነድ ያቅርቡ። ለሁሉም ስብሰባዎች እና ሰነዶች እንዳስፈላጊነቱ የትርጉም ወይም የማስተርጎም አገልግሎት ያቅርቡ።

**2** የተማሪዎን አስተማሪ፣ ጉዳይ አስተዳዳሪ እና ዳይሬክተር ያግኙ። ስጋቶችዎን እና ጥያቄዎችዎን በጽሁፍ ያቅርቡ። የሰበሰቡትን ማንኛውንም ውሂብ ያካትቱ።

**3** ከተማሪዎ ቡድን ጋር IEP መርሐግብር ያስይዙ። የፕሮግራም ልዩ ባለሞያውን በማካተት። የወላጅነት ስጋትዎን ለሁሉም የ IEP አባላት ከስብሰበው ቀድመው ይላኩ።

**4** ከ IEP ስብሰባ በኋላ የተማሪዎ ፍላጎት እየተሟላ ካልሆነ ክልላዊ ተቆጣጣሪውን ያግኙ።

**5** አሰሳሳቢ ለሆኑ ጉዳዮች መፍትሄ ለመስጠት ከዲስትሪክት እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር ስብሰባ ይጠየቁ። ይህ በጽሁፍ መቀመጡን እርግጠኛ ይሁኑ። የሚያሰፈልግ ከሆነ ትርጉም እና ማስተርጎም አገልግሎት ይጠይቁ።

**6** የተቀናጀ የ IEP ስብሰባ ከ Sounds Options Group ጋር ለ 800-692-2540 በመደወል።

ዲስትሪክቱን በተደጋጋሚ አግኝተውም የእርስዎ ተማሪ አሁንም ተግዳሮቶች ያሉበት ከሆነ፣ ቀጣዩ እርምጃ መደበኛ ቅሬታ እንደሚከተለው ማቅረብ ይሆና፤

**7** **በ OSPI በኩል የልዩ ትምህርት ቅሬታ፦** በዚህ ሂደት በኩል ብዙ ውጤቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡

- በ OSPI የቅሬታ ሂደት በኩል ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ሳያስፈልግ በቅሬታው እና በዲስትሪክቱ መካከል ስምምነት ላይ ሊደረስ ይችላል።
- OSPI በቅሬታው ላይ ለተነሱት ጉዳዮች እንዴት አድርጎ የእርምት እርምጃዎችን እንደሚወስድ ይገልጻል።
- OSPI ዲስትሪክቱ ምንም እንዳላጠፋ ያውቃል እና ምንም እርምጃ አይወሰድም።

**8** **ማስታረቅ፤** ገለለልተኛ የሆነ ሶስተኛ ወገነን በመጠቀም ወላጆች እና የዲስትሪክት ሰራተኛ ተገናኝተው ለስጋቶች መፍትሄ የሚሰጡበት በፈቃደኝነት የሆነ ሂደት።

- በእርቁ ጊዜ የሚካሄደው ንግግር ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ነው።
- ስምምነት ላይ መደረስ ከተቻለ፣ በጽሁፍ ሊቀመጠ እና በሁለቱም ወገኖች ሊፈረምበት ያስፈልጋል። ይህ ስምምነት አስገዳጅ ነው። ዲስትሪክቱ ስምምነቱን ለመፈጸም የማይችል ከሆነ ወላጅ ወይም ህጋዊ አሳዳጊ የማህበረሰብ ቅሬታን ወይም የፍርድ ቤት ክስን ሊያስገባ ይችላል።

**9** **የችሎት ሂደት ጥያቄ**

- መደበኛ የሆነ ህጋዊ ሂደት ሲሆን በአስተዳዳሪ የህግ ዳኛ የሚመራ ይሆናል። በአጠቃላይ ይህ ካሉት ውስጥ ውስብስብ የሆነው አማራጭ ነው። ጠበቃ ሊያስፈልግዎ ይችላል።

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## በብዛት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች

### በ 504 እቅድ እና በIEP መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

የ 504 እቅድ እና IEP ሁለቱም መደበኛ የሆኑ በተማሪው የትምህርት ቡድን የተማሪውን ፍላፎት ለሚሟላት እና መገለልን ለማስወገድ የሚፈጠሩ እቅዶች ናቸው። ነገር ግን ሁለቱም የየራሳቸው መስፈርት እና ጥበቃዎች ያላቸው የተለያዩ ሰነዶቸ ናቸው። 504 እቅድ አነስ ያለ IEP አይደለም።

| IEP | 504 እቅድ |
|---|---|
| ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም | የመማሪያ አካባቢን ለመደረስ እርግጠኛ የሚያደርግ እቅድ |
| ተማሪው በግምገማ መሰረት ትምህርታቸውን “ለመድረስ” የሚያስፈልጋቸው ነገር ዝርዝር ማለትም በውሂብ ላይ የተመሰተ በልዩ መንገድ የተዘጋጀ መመሪያን (SDI) ያካትታል። | የአገልግሎቶችን፣ ድጋፎችን እና ለ FAPE መዳረሻን የሚሰጡ ነገርግን የትምህርት ኢላማውን የማየቀይሩ ዝረዝር |
| IDEA ሂደታዊ ጥበቃዎች የወላጆችን፣ ተማሪዎችን እና ግምገማዎችን መብት ለማስጠበቅ | ክፍል 504 ሂደታዊ ደህንነት ማስጠበቂያዎች፣ ይበልጥ የተደገበ |
| በ IDEA መሰረት ወላጅ ንቁ የ IEP አባል እንዲሆን ይጠይቃል | የወላጅ ስምምነት የ 504 እቅድን ከማስቀመጥ በፊት ያስፈልጋል |
| አንደ IDEA መሰረት በ2-3 አመታት ውስጥ ለልጁ ዳግም ምርመራ ያስገድዳል | የውሂብ እና መዝገቦች ግምገማዎችን ይጠቀሙ፣ መደበኛ ግምገማ ምንም አያስፈልግም |
| በወሂብ መሰረት የሂደት ግምገማ አስፈላጊ ነው | ምንም አይነት የሂደት ግምገማ አያስፈልግም |
| በአገልግሎት ነክ እና ትምህርት ነክ ግቦች ዙሪያ ይገነባል | ምንም ግቦች የሉም |

### በአቀማመጥ እና ምደባ መሃል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

አቀማመጥ በአካል ጉዳይ ባለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ህግ (IDEA) ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ውስን ቃል ነው ስለዚህም በልዩ ትምህርት አገባብ ፣በመላው ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ተመሳሳይ ትርጉም አለው። አቀማመጥ ልዩ የአስተምህሮ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልግ መርሃ-ግብር፣ ህንጻዎች፣ የሰው ሃይል፣ ቦታ ወይም መሳሪያ ያካትታል። አቀማመጥ የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች እንዳለ የሚቀርቡ የተያያዙ አገለግሎቶችን ያካትታል። የተማሪ ምደባ የሚማሩበት ትምህርት ቤት ቦታ ነው። ወረዳው ምደባን የሚወስነው የተማሪውን አቀማመጥ እና አገልግሎቶች በግምት ውስጥ ካስገቡ በኋላ ነው። ሲቻል እና ተገቢ ሲሆን፣ ልዩ የአስተምርሆ አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች በሰፈራቸው ባለ ትምህርት ቤት ውስጥ አገልግሎት ያገኛሉ። አንዳንድ ተማሪዎች በአገልግሎቶቻቸው ውስብስብነት ምክንያት የተሻሻሉ የትምህርት ነክ ስራዎች ሊኖሯቸው ይችላል።

### አንድ ተማሪ የት ነው አገልግሎቶቹን የሚያገኘው?

ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ተማሪ በተራቀቀ ትንሹ ወሳኝ ስፍራ (LRE) ውስጥ አገልግሎት ያገኛሉ። ይህም በጠቅላላው የትምህርት ምቼት ወይም በሌላ ክፍል የወጣ የአንድ ለአንድ ምቹት ወይም በትንሽ ቡድን ውስጥ ሊሆን ይችላል።

### ተማሪዬ ለልዩ የአስተምርሆ አገልግሎት ለመካተት በህክምና ለይቶ የታወቀ የአካል ጉዳት ያስፈልገዋል?

አይ፣ ተማሪ ለመገምገም የህክምና ለይቶ እውቅና አያስፈልገውም።

Seattle Special Education PTSA

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## በብዛት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች

### ቀዳሚ የአገልግሎት መንገዶች ምንድን ናቸው?

የሲዓትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች (SPS) ለSPS የተወሰነ ቁጥር ያላቸው “ቀዳሚ አገልግሎቶች” መንገዶች ለይቷል። እነዚህ የተወሰኑ ልዩነቶች ለተማሪው የትምህርት ነክ ስራ እና ለአስተማሪ ሙያዊ እድገት መገመት የሚችሉ መንገዶች/ምርጫዎች ይፈጥራሉ። እነዚህ የቀዳሚ የአገልግሎት አይነት ገለጻዎች በሲዓትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ከK-12 ክፍሎች፣ በሚማሩ ተማሪዎች እና የልዩ የአስተምርሆ ለውጥ አገልግሎቶችን የሚያገኙ(እስከ 21 አመት ድረስ) ተማሪዎች ላይ ተግባራዊ የሚሆን ነው።

### የተያያዙ የትምህርት ቤቶች ግራፍ ለ 2021-22 (በቅርቡ የዘመነው 6/1/2021)

የተያያዙ ትምህርት ቤቶች ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

የተያያዙ ትምህርት ቤቶች ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

የተያያዙ ትምህርት ቤቶች ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

### የSPS ቀዳሚ አገልግሎቶች መንገዶች እንዴት ነው የሚወሰኑት?

| የአገልግሎት መንገድ | ገለጻ |
|---|---|
| ሃብት | ተማሪዎች ከቀላል እስከ መለስተኛ የምሪት ፍላጎት ልዩነቶቻቸውን ውስን የትምህርት ፍላጎቶቻቸው እና ማህበራዊ ችሎቶቻችውን የሚያዳርስ ተራቆ የተዘጋጀ መመሪያ (SDI) ያገኛሉ። እነዚህ ተማሪዎች አብዛኛውን የምሪት ጊዜያቸውን በጠቅላላ የትምህርት ነክ መቼት ውስጥ ከ ግብ ባለው ድጋፍ ጋር ያሳልፋሉ።+* |
| ማግኘት | የበለጠ ሃብት የሚፈልጉ አገልግሎት የሚያድፈልጓቸው ተማሪዎች። እነርሱ ከመለስተኛ እስከ ከፍተኛ የትምህርት እና አገልግሎት ፍላጎቶችን የሚያዳርስ ተራቆ የተዘጋጀ መመሪያ **(SDI)** ያገኛሉ። እነዚህ ተማሪዎች አብዛኛውን የመምሪያ ጊዜያቸውን በጠቅላላ የትምህርት መቼት ውስጥ አያሳለፉ በ**IEP** ግቦቻቸው ላይ ሂደት ማድረግ ይችላሉ። የአነስተኛ ቡድን መመሪያ እና ጣልቃ ገብነትን ጨምሮ እነዚህ ተማሪዎች ከተለያዩ የተራቀቁ መመሪያዎች ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ። *+ |
| ትኩረት | ከፍተኛ የትምህርት እና የአገልግሎት ፍላጎቶቻቸውን ለማዳረስ ተራቆ የተዘጋጀ መመሪያ (SDI) የሚያገኙ ተማሪዎች። በተራቆ የተዘጋጀ መመሪያ ተማሪዎች በጠቅላላው የትምህርት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ለመሳተፍ እድሎች ይኖራቸዋል። እነዚህ ተማሪዎች አብዛኛውን የመመሪያ ጊዜያቸውን በአነስተኛ ቡድን መቼት እንደ ትንሹ ውስን ቦታ (LRE) ሆኖ ጊዜ በማሳለፋቸው ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ፣ ነገር ግን ይሄ በIEP ሊለያይ ይችላል።* |
| ማህበራዊ/ስሜታዊ | የማህበራዊ/ስሜታዊ ክህሎቶችች፣ ሂደቶች እና መረዳትን እድገት እንዲረዳ ተራቆ የተዘጋጀ መመሪያ (SDI) የሚያገኙ ተማሪዎች። ተማሪዎች በተማሪው **IEP** እንደሚወሰነው በ **SDI** ውስጥ የተወሰነውን ወይም ሁሉንም የትምህርት መመሪያዎች ሊያገኙ ይችላሉ። በአብዛኛውን ጊዜ አገልግሎቶች በትንሽ ቡድን መቼት ውስጥ ነው የሚሰጡት፣ ነገር ግን ይህ በIEP ሊለያይ ይችላል።* |
| ልዩ | ከጠቅላላው የትምህርት መርሃ ግብር በሰፊው የሚለይ የትምህርት መርሃ ግብር ጥቅም የሚያገኙ ተማሪዎች። ተራቀው የተዘጋጀ መመሪያ (SDI) ትምህርት ነክ፣ የንግግር፣ የህይወት እና አገልግሎት ችሎታ አካላትን ሊያካትት ይችላል። በአብዛኛውን ጊዜ አገልግሎቶች በትንሽ ቡድን መቼት ውስጥ ነው የሚሰጡት፣ ነገር ግን ይህ በIEP ሊለያይ ይችላል።* |

+በተማሪው IEP መሰረት አገልግሎቶች በየትኛውም መቼት ውስጥ ሊሰጡ ይችላሉ።
*ይህ የመጀመሪያ የአገልግሎት አይነት በየትኛውም የIDEA የአካል ጉዳተኛ ምድብ ውስጥ ለሚካተቱ ተማሪዎች ይቀርባል።

ግራፍ ቀጣዩ ገጽ ላይ ይቀጥላል ▶ ▶

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## በብዛት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች

| የአገልግሎት መንገድ | ገለጻ |
|---|---|
| መስማት የተሳናቸው/ ለመስማት የሚከብዳቸው (DHH) | በIEP ቡድናቸው እንደሚወሰነው በትንሹ የሚገድብ ቦታ (LRE) ተራቆ የተዘጋጀ መመሪያ (SDI) የሚያገኙ ተማሪዎች። የመመሪያ ይዘታ ስምምነቶች፣ ለውጦች እና የአስተርጓሚ አግልግሎቶች ባሉት ተራቆ በተዘጋጀ መመሪያ ተማሪዎች በጠቅላላው የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ የመሳተፍ እድሎች ያቀርባል። ተማሪዎች ከምደባ ቦታቸው ውጪ ባሉ የእርዳታ አገልግሎቶች ወይም የተራቀቁ መሳሪያዎች መሰባሰብ ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ አገልግሎት መስማት ለተሳናቸው ወይም መስማት ለሚከብዳቸው ተማሪዎች ክፍት ነው። |
| አላማ | ተማሪዎች በIEP ቡድናቸው እንደሚወሰነው በትንሹ የሚገድብ ቦታ(LRE) ተራቆ የተዘጋጀ መመሪያ (SDI) ያገኛሉ። የመመሪያ ይዘት እንደ አይታ እና እንቅስቃሴ ***(O** እና **M)*** እና እንደ ብሬል አይነት የእይታ አገልግሎቶች አይነት እርዳታዎች እና ማሻሻያዎች ባሉት ተራቆ በተዘጋጀ ስርዓተ ትምህርት ለተማሪዎች በጠቅላላው የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ የመሳተፍ እድሎች ያቀርባል። ተማሪዎች ከምደባ ቦታቸው ውጪ ባሉ የእርዳታ አገልግሎቶች ወይም የተራቀቁ መሳሪያዎች መሰባሰብ ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ አገልግሎት ማየት ለተሳናቸው ወይም ማየት ለሚከብዳቸው ተማሪዎች ክፍት ነው። |
| በሕክምና ደካማ | ተማሪዎች በIEP ቡድናቸው እንደሚወሰነው በትንሹ የሚገድብ ቦታ(LRE) ተራቆ የተዘጋጀ መመሪያ (SDI) ያገኛሉ። የመመሪያ ይዘታ ተራቆ በተዘጋጀ መመሪያ ተማሪዎችበጠቅላላው የትምህርት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ የመሳተፍ እድሎችን ያቀርባል። ተማሪዎች ከምደባ ቦታቸው ውጪ ባሉ የእርዳታ አገልግሎቶች ወይም የተራቀቁ መሳሪያዎች መሰባሰብ ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ። በአብዛኛው ጊዜ አገልግሎቶች በትንሽ ቡድን መቼት ውስጥ ነው የሚሰጡት፣ ነገር ግን ይህ በIEP ሊለያይ ይችላል። ይህ አገልግሎት ከፍተኛ የህክምና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ከሁሉም የIDEA አካል ጉዳት ምድብ ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ክፍት ነው። |
| 18-21 የለውጥ አገልግሎቶች | በለውጥ አገልግሎቶች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ 18-21 አመት ድረስ ለከፍተኛ የአገልግሎት ፍላጎቶች ላሏቸው ተማሪዎች ተራቆ የተዘጋች መመሪያ ያገኛሉ።ይህ አገልግሎት እድሜያቸው ከ18-21 አመት ድረስ ላሉ፣ ለየትኛውም IDEA የአካል ጉዳት ምድብ ለሚገኙ ተማሪዎች ክፍት ነው። |

ከ https://www.seattleschools.org/departments/special-education/services/placement-and-primary-service-types/ በ 4/5/22 የተወሰደ

+በተማሪው IEP መሰረት አገልግሎቶች በየትኛውም መቼት ውስጥ ሊሰጡ ይችላሉ።

*ይህ የመጀመሪያ የአገልግሎት አይነት በየትኛውም የIDEA የአካል ጉዳተኛ ምድብ ውስጥ ለሚካተቱ ተማሪዎች ይቀርባል።

### ተማሪዬ IEP ከተተገበረ በኋል ምንም ለውጥ እያሳየ አይደለም። አሁን ምን ማድረግ እችላለሁ?

ስለ ሃሳቦቻቹ የተማሪዎ ጉዳይ ሃላፊን ያግኙ እና የIEP ስብሰባ ይጥሩ። በስብሰባው ላይ፣ ስለሚያሳስብዎት ነገር ተወያዩ እና አስፈላጊ ከሆነ የIEP ን ማሻሻል ሃሳብ ያቅርቡ።

### ተማሪ በአመት አንድ የ IEP ስብሰባ ብቻ ነው የሚፈቀደው?

አይ። ወላጅ የIEP ስብሰባን በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላል። ጥያቄዎን እና የ IEP ስብሰባ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች በጽሁፍ ያስቀምጡ። አውራጃው ተማሪው ከ IEP ቡድን ውይይት ተጠቃሚ እንደሚሆን ከተስማሙ እና ወይ የስብሰባ ጊዜ እና ቀን በማሳየት ወደፊት ይራመዳል ወይም ችግሮቹን ለመፍታት አማራጭን ይመክራል። አንድ ወረዳ የIEP ስብሰባ ለመጥራት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ እምቢተኝነታቸውን በPWN ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

### ለ IEP ስብሰባ እንዴት መዘጋጀት አለብኝ?

የቀደመውን የIEP እና የሂደት ሪፖርቶችን ይገምግሙ። ጥያቄዎችዎን እና ስጋቶችዎን አስቀድመው ያዘጋጁ።

በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች በሚቀጥለው ገጽ ላይ ይቀጥላል ▶▶

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## በብዛት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች

### አውራጃው ተማሪዬ ለ IEP ብቁ እንዳልሆነ ቢገልጽስ?

ምክንያቱን በጽሁፍ ማቅረብ አለበት። ይህ አብዛኛው ጊዜ በPWN ውስጥ ይሆናል። በግምገማው ውጤት ካልተስማሙ በስብሰባው ላይ እንደተሳተፉ እና በግምገማው ውጤት እንደማይስማሙ መፃፍዎን ያረጋግጡ።

### በ IEP ውስጥ ምን ያህል ግቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገደብ አለ?

አይ፣ ግቦች በተማሪ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ናቸው እንጂ የትምህርት ቤት ግብዓቶች አይደሉም።

### የ IEP ማሻሻያ ምንድን ነው?

የIEP ማሻሻያ በ IEP ላይ የሚደረግ ትንሽ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ነው። ሁሉም ወገኖች ከተስማሙ ማሻሻያ ለማድረግ ሙሉ የIEP ቡድን የግብአት ስብሰባ አያስፈልግም። ማንኛውም ለውጦች ከመደረጉ በፊት የተጠቆመው ማሻሻያ በ PWN ውስጥ እንዲቀመጥ ይመከራል።

### የ IEP ቁሳቁሶች ከስብሰባ በፊት ካልተሰጡኝ ወይም በቂ ጊዜ ካልተሰጡኝ ከስብሰባ በፊት እነሱን ለመገምገም ጊዜ ካገኘሁ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ወላጆች እና አሳዳጊዎች በትምህርት ዓመቱ ውስጥ በተለይም ከ IEP ስብሰባ በፊት መዝገቦችን የመመርመር እና የመገምገም መብት አላቸው። መዝገቦቹን ለማየት ጥያቄ ካቀረቡ እና ካልተሰጡ የትምህርት ቤቱን ርእሰ መምህር እና የክልል ተቆጣጣሪን ያነጋግሩ። መዝገቦቹን እና ሰነዶችን ለመገምገም ጊዜ ካገኙ በኋላ ስብሰባው ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ መጠየቅ ይችላሉ።

### በግምገማው ውጤት ካልተስማማሁስ?

ስጋትዎን በጽሁፍ ያስቀምጡ። እንዲሁም IEE ወይም ገለልተኛ የትምህርት ግምገማ መጠየቅ ይችላሉ። አውራጃው IEE ለማግኘት እንዲረዳዎ መረጃ የመስጠት ሃላፊነት አለበት።

### }ለገለልተኛ የትምህርት ግምገማ (IEE) የሚከፍለው ማነው?

ወላጅ ወይም አሳዳጊ የ IEE ወጪዎችን መሸፈን አለባቸው። ነገር ግን፣ በህዝብ ወጪ IEEን መጠየቅ ትችላለህ፣ ነገር ግን ድስትሪክቱ በጥያቄህ ካልተስማማ በስተቀር የፍትህ ሂደትን ይጠይቃል።

### የ 504 እቅድ ያወጣው ማነው?

የልጁን ፍላጎት የሚያውቅ እና የሚረዳ እና መረጃውን እና መረጃውን ከግምገማዎች መተርጎም የሚችል የግለሰቦች ቡድን። በአጠቃላይ፣ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ አጠቃላይ ትምህርት መምህር(ዎች)፣ 504 አስተባባሪዎች (ዎች) እና የት/ቤት አስተዳዳሪ በ504 እቅድ ውስጥ ይሳተፋሉ።

### በ 504 እቅድ ውስጥ ምን ይካተታል?

የ 504 እቅድ ብዙውን ጊዜ ለልጁ ማረፊያዎችን እና ድጋፎችን እንዲሁም እነዚህን ድጋፎች ማን እንደሚሰጥ እና እንደሚከታተል ያካትታል።

### የእኔ ተማሪ 504 እቅድ ካለው፣ የልዩ ትምህርት አገልግሎትን እንደ ተማሪ ይቆጠራሉ?

አይደለም የልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚቀበል ተማሪ የ504 እቅድ ሳይሆን IEP አለው። ስንል ግን አሁንም እያካተትናቸው ነው።"ልዩ ትምህርት ተማሪዎች።"

Seattle Special Education PTSA

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## በብዛት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች

### የተራዘመ የትምህርት ዘመን (ESY) አገልግሎቶችን ለተማሪዬ እንዴት እጠይቃለሁ?

በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ጥያቄዎን በጽሁፍ ያስቀምጡ። ተማሪዎ ከሆነ የ IEP ስብሰባ በዓመቱ መጀመሪያ ላይ የታቀደ ነው፣ በ IEP ስብሰባ ላይ ስለ ESY ለመወያየት ይጠይቁ። ያለበለዚያ ስለESY ለመወያየት የIEP ስብሰባ ይጠይቁ።

### ለ IEP ስብሰባ በተመደበው ጊዜ ሁሉንም ስጋቶቻችንን ካልመለስንስ?

ውይይቶች ካለ በኋለኛው ቀን ሊቀርቡ እና ሊታዘዙ ይችላሉ። በስብሰባው ወቅት በቂ ጊዜ። የአሁኑ ስብሰባ ከማብቃቱ በፊት የIEP ስብሰባ ቀጣይ መርሐግብር መያዙን ያረጋግጡ።

### በተማሪዬ ከሌሎች ጋር እንዴት መገናኘት እችላለሁ? ተመሳሳይ ልምዶችን የሚጋሩ ትምህርት ቤት?

የሲያትል ልዩ ትምህርት PTSA የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ኮሚቴን ያግኙ እና ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ለመገናኘት ድጋፍ ይጠይቁ። እንዲሁም የአካባቢዎን PTA ወይም የትምህርት ቤት ርእሰ መምህርን ማነጋገር ይችላሉ።

### አውራጃው ግምገማ ለመስጠት ከተስማማ ምን ማድረግ አለብኝ?

ልጅዎ ችግር አለበት ብለው በሚያምኑባቸው በሁሉም ዘርፎች የትምህርት ቤቱ የስነ-ልቦና ባለሙያ ስለሚያሳስብዎት ነገር እንደሚያውቅ ማረጋገጥ አለብዎት። የግምገማውን ግልባጭ ከስብሰባው ከበርካታ ቀናት በፊት መጠየቅዎን ያረጋግጡ ስለዚህ እሱን ለመገምገም እድሉ እንዲኖርዎት። የግምገማውን ፈቃድ በጥንቃቄ ያንብቡ እና ካልተረዱ ጥያቄዎችን ይጠይቁ። የስምምነት ቅጹን ይፈርሙ እና ወደ ትምህርት ቤቱ ይመልሱት።

### በ IEP ስብሰባ ላይ የሚካፈለው ማነው?

ወላጆች/ተንከባካቢዎች እና ተማሪዎ ተገቢ ከሆነ ከትምህርት ቤቱ ቡድን ጋር ከጉዳዩ አስተዳዳሪ፣ ልዩ ትምህርት መምህራን፣ አጠቃላይ ትምህርት መምህራን፣ ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች (OT፣ PT፣ SLP)፣ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ፣ የዲስትሪክት አስተዳዳሪ (እንደ አስፈላጊነቱ) , የሽግግር ሰራተኞች እና የልጅዎ ባለሙያ ናቸው ብለው የሚያምኑት ማንኛውም ሰው ብዙውን ጊዜ የግል ቴራፒስቶች ናቸው። እንዲሁም በስብሰባው ላይ ማስታወሻ አቅራቢን መጠየቅ ይችላሉ። በሚቻልበት ጊዜ የራስዎን ማስታወሻ ደብተር ይዘው እንዲመጡ ይመከራል። ወላጅ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ሰው ወደ IEP ስብሰባ ማምጣት ይችላሉ። ከተቻለ በእርግጠኝነት ጓደኛ ወይም የቤተሰብ አባል ይዘው ይምጡ።

### ምንድን በ SIT ቡድን እና በ IEP ቡድን መካከል ያለው ልዩነት ነው?

የSIT ወይም የተማሪ ጣልቃ ገብነት ቡድን በግምገማዎች ውስጥ ይሳተፋል እና በ 504 እቅድ ውስጥ የተካተቱትን ድጋፎች ያዘጋጃል። የ IEP ቡድን የልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ ተማሪዎችን የግለሰብ ትምህርት እቅድ ያስተዳድራል እና ያዘጋጃል።

### ድጋሚ ግምገማዎች መቼ ነው የሚካሄዱት?

ቢያንስ በየ 3 ዓመቱ። ግምገማ በማንኛውም ጊዜ በ IEP ቡድን አባል ሊጠየቅ ይችላል ነገር ግን በ IEP ቡድን አባላት ስምምነት ላይ የተመሰረተ ፍላጎት ከሌለ በስተቀር አውራጃው አንዱን የማጠናቀቅ ግዴታ የለበትም።

### የተማሪዬ ትምህርት ቤት ተማሪዬ የሚያስፈልገውን ልዩ የትምህርት “ፕሮግራም” ባይኖረውስ?

የአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ይሁን አልሆነ ተማሪው የተመደበበትን ፕሮግራም በሚያቀርብ ትምህርት ቤት SPS እንዲማር ይፈልጋል። ወላጆች በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት እንዲመደብላቸው የመቃወም እና የመጠየቅ መብት አላቸው። ድስትሪክቱ ይህን ጥያቄ ውድቅ ካደረገ፣ ወላጅ ዳኛ ውሳኔ እንዲሰጥ የፍትህ ሂደትን መከተል ይችላል።

Seattle Special Education PTSA

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## በብዛት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች

### በጣም ጥሩ የግል ረዳት አለኝ። ተማሪዬን በትምህርት ቤት ሊረዱኝ ይችላሉ?

ይህ በትምህርት ቤቱ ውሳኔ ነው። ጥያቄዎን በጽሁፍ ያስቀምጡ እና ምላሻቸውን በቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ (PWN) ውስጥ ይጠይቁ። አውራጃው ነፃ እና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) እንዲሰጥ ይጠበቅበታል ስለዚህ ሌላው አማራጭ የ FAPE መዳረሻን የሚከለክል ከሆነ ድስትሪክቱ ድጋፉን እንዲሰጥ መጠየቅ ነው።

### ትምህርት ቤቱ ልጄን ማገድ ወይም ማግለል የተፈቀደለት መቼ ነው?

መመሪያ #3246፣"ማግለል መጠቀም በሁሉም ሁኔታዎች የተከለከለ ነው። በአንድ ሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ሊደርስ የሚችልበት ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር በተማሪዎች ላይ እገዳዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው። በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች፣ መገደብ በተማሪው ወይም በሌሎች ላይ የሚደርሰውን የአካል ጉዳት ለመከላከል ወይም ለመቀነስ እንደ የመጨረሻ አማራጭ ብቻ ሊያገለግል ይችላል። ከባድ የአካል ጉዳት የመከሰቱ አጋጣሚ ከሌለ የእገዳን ወይም ሌላ የአካል ቀውስ ጣልቃ ገብነትን መጠቀም ወዲያውኑ መቋረጥ አለበት። በምንም አይነት ሁኔታ እነዚህ ቴክኒኮች እንደ ተግሣጽ፣ ቅጣት፣ ለአዋቂዎች ምቾት፣ ወይም ለንብረት ውድመት ምላሽ ወይም ለአካል ጉዳት የማያጋልጥ የተማሪ መስተጓጎል ጥቅም ላይ አይውሉም።" https://www.seattleschools.org/wp-content/uploads/2021/07/3246.pdf

### የአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮቶኮል (ERP) ምንድን ነው?

ይህ አስቀድሞ ለሚጠበቁ "ከባድ የአካል ጉዳት የሚያስከትሉ ሊቀሩ የማይችሉ ድንገተኛ አደጋዎች" የተቀመጠ የምላሽ እቅድ ነው። እንደ ወላጅ ወይም ተንከባካቢ፣ በ IEP ማህደር ውስጥ ያለውን መስማማትዎን የሚያመለክት ሳጥን ላይ ምልክት በማድረግ የ ERP እቅድ እንዲኖርዎት መምረጥ ወይም ሳጥኑ ላይ ምልክት ሳያደርጉ ለመውጣት መምረጥ ይችላሉ። "የአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮቶኮሎች፣ ከተዘጋጁ ፣በተማሪው IEP ውስጥ መካተት እና በየዓመቱ መገምገም አለባቸው። የአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮቶኮሎች የታለመ ባህሪን ለመለወጥ፣ ለመተካት፣ ለማስተካከል ወይም ለማጥፋት የታለመውን የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ የዘዴ አጠቃቀምን ለመተካት ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም። የአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮቶኮሎች ነፃ፣ ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) እና የአደጋ ምላሽ ፕሮቶኮሎችን ከማፅደቁ በፊት የወላጅ ስምምነትን በቅድሚያ ተቀብሎ ለማቅረብ የሚያስፈልገውን የላቀ የትምህርት ዕቅድ ይመዘግባሉ።"

https://www.seattleschools.org/wp-content/uploads/2021/09/3246SP.pdf

### ትርጉም ያለው የወላጅ ተሳትፎ ምን ይመስላል?

ስብሰባዎችን አስቀድሞ ማሳወቅን፣ የትምህርት መዝገቦችን ማግኘትን፣ ወላጆችን በልጃቸው ትምህርት ውስጥ እንደ አባሪዎች እና አጋሮች ማክበርን፣ ልጃቸውን በትምህርት ቤት አካባቢ የመመልከት እድልን እና የወላጅ ስምምነትን ማካተት አለበት።

### ተማሪዬ በ IEP ስብሰባቸው መሳተፍ ይችላል?

አዎ! በተገቢው ሁኔታ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ። ስለ ግቦቻቸው፣ ድጋፎቻቸው፣ እና ጠንካራ ጎኖቻቸው በማሳተፍ አስቀድመው ይጀምሩ። እና ሰራተኞችን ከተማሪዎች በተደጋጋሚ አስተያየት እንዲፈልጉ ያበረታቱ።

Seattle Special Education PTSA

# የትምህርት ቤት ቅጣት

## የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚጠቀሙባቸው የቅጣት ዓይነቶች

### ምንድን ነው?

በትምህርት ቤት አካባቢ፣ "ቅጣት" የሚተገበረው ለሥነምግባር ጥሰት ምላሽ ነው። የዲሲፕሊን ግብ ከመቅጣት ይልቅ ማስተማር መሆን አለበት።

**የቅጣት አለመመጣጠን፦** የአፍሪካዊ አሜሪካውያን ተማሪዎች እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከነጮች፣ ከኒውሮቲፒካል(neurotypical) እኩዮቻቸው በተለየ በከፍተኛ መጠን እንደሚቀጡ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ቅጣት በግለሰብ ተማሪዎች ላይ በሚተላለፍበት ጊዜ፣ በስርዐት ደረጃ በመጨረሻ ግቡ ላይ መድረስ ያለበት፣ ተግባር ነው።

**በጣም ጥሩ የቅጣት እርምጃዎች** ተማሪዎችን ወደ ባህሪ ጥሰት የሚወስዱ ችግሮችን በመፍታት ዙርያ ተከላካይ፣ ንቁ እና ማዕከላዊ ናቸው። በጣም ጥሩ የተማሪ ውጤቶች የሚከሰቱት ተማሪዎች ደህንነት በሚሰማቸው እና በሚታዩበት ጊዜ፣ እንደ ንቁ ተሳታፊዎች በራሳቸው ትምህርት ሲሳተፉ፣ ደጋፊ በሆኑ ግንኙነቶች ውስጥ፣ እና "ልጆች ከቻሉ ጥሩ ይሰራሉ" የሚለውን በመረዳት ነው **(Ross Greene)**[1]።

### በSPS መቀጣት

SPS አስተዳዳሪዎች ለባህሪ ጥሰት ተገቢውን የቅጣት ምላሾችን እንዲመርጡ ለመምራት **የቅጣት አባሪ**[2] ይከተላሉ። በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች **የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች**[3] ሰነድ ላይ እንደተገለጸው፣ "ተማሪዎች፣ ወላጆች እና አሳዳጊዎች ትምህርት ቤቱ በዲሲፕሊን ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ከመግባቱ በፊት ግብአት በመስጠት ንቁ አጋሮች የመሆን መብት አላቸው።"

### የቅጣት እርምጃዎች የሚያካትቱት፦

ትንሹ እገዳ → ትልቁ እገዳ

- **የመማሪያ ክፍል ምላሽ፦** በክፍል አስተማሪ የሚያዝ
- **የትምህርት ቤት ምላሽ፦** በትምህርት ቤት አስተዳዳሪ(ዎች) የሚያዝ፤ ሊያካትት የሚችለው፦
- **የትምህርት ቤት እገዳ፦** ከክፍል መውጣት፣ ነገር ግን በግቢው መቆየት ይችላል
- **ቀደም ብሎ መባረር፦** አንድ ትምህርት ቤት ወላጅ/አሳዳጊ በባህሪ ምክንያት ልጅ እንዲወስድ ሲጠይቅ፤ እንደ የአጭር ጊዜ እገዳ መመዝገብ አለበት
- **የአጭር ጊዜ እገዳ፦** በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እስከ 10 ቀናት ድረስ እንዲገኙ አይፈቀድም
- **የረጅም ጊዜ እገዳ፦** በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ከ10 ቀናት በላይ እንዲገኙ አይፈቀድም
- **ማባረር፦** በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ አይፈቀድም፤ ለትምህርት የጊዜ ቆይታ ድረስ ሊቆይ ይችላል፤ በመሳሪያዎች ምክኒያት ካልሆነ በስተቀር ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ሊተገበር አይችልም

- ለIEP/504 ተማሪዎች ተጨማሪ የቅጣት ጥበቃዎች (እና 504 እንደሚያስፈልጋቸው ገና ያልተለዩ)፦ የተግባር የባህሪ ግምገማዎችን ያካትታሉ **(FBAs)**[4]፣ የባህሪ ጣልቃ ገብነት ዕቅዶች **(BIPs)**[5]፣ የመገለጫ መወሰኛ ግምገማ **(MDRs)**[6]፣ ጊዜያዊ አማራጭ ትምህርታዊ ምደባዎች (ከጦር መሳሪያዎች፣ ህገወጥ መድሃኒቶች እና/ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ጋር በተያያዘ የስነምግባር ጥሰት ለሚፈጽሙ ተማሪዎች)። ትምህርት ቤቶች ከቅጣት ወይም ከልከላ ቅጣት እንዲርቁ የሚያግዙ የባህሪ ጥሰት ችግሮችን የሚፈቱ ብዙ መሳሪያዎች በአመራራቸው ላይ አሏቸው።

- **በአሰቃቂ ሁኔታ መረጃ ያለው ልምምድ**[7]
- **እንደገና የመመለስ ፍርድ**
- **ችግር ፈቺ ሞዴሎች**[9]
- **የOSPI ባህሪ በጣም ጥሩ ልምምዶች ዝርዝር**[10]

*ስለ FBA እና BIP ያሉ ስጋቶች፦ ለተማሪው ጥበቃ እንዲሆኑ የታሰቡ ቢሆንም፣ የFBA እና የBIP ብዙውን ጊዜ እንደ የስሜት ጫና ወይም ጉዳት ላሉ፣ወደ ቅጣት እርምጃ የሚመሩ የባህሪ ውጤቶች እንደ መሰረታዊ ሁኔታዎች አይቆጠሩም።

Seattle Special Education PTSA

# የትምህርት ቤት ቅጣት

## የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚጠቀሙባቸው የቅጣት ዓይነቶች

- በእገዳ ጊዜ የትምህርት አገልግሎቶች*:- የዲሲፕሊን ርምጃው ምንም ያክል ቢሆን ለተማሪዎች በማንኛውም እና በሁሉም እገዳዎች እና መባረሮች ትምህርታዊ አገልግሎቶችን መስጠት አለባቸው። እነዚህ አገልግሎቶች ተማሪው አጠቃላይ የትምህርት ስርአተ ትምህርቱን እንዲያገኝ መፍቀድ እና ተማሪው ወደ IEP ግቦቹ  መሻሻል እንዲያደርግ መደገፍ አለበት።

**የተነገረ ግጭት ሲከሰት**

(!) ለወላጆች/ተንከባካቢዎች የቅጣት እርምጃ ማሳወቂያ እርምጃው ከተወሰነበት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።

(!) ተማሪው በዲሲፕሊን ሂደት ውስጥ የወላጅ ተሳትፎ የማግኘት መብት አለው። ለአጭር ጊዜ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ሲደረግ ወላጆቻቸውን እንዲያነጋግሩ ሊፈቀድላቸው ይገባል።

**ደረጃ 1**

**የመጀመሪያ ችሎት እና የመጀመሪያ ማሳወቂያ**

መታገድ ወይም መባረር ከመፈጸሙ በፊት፣ የSPS ሰራተኛ መደበኛ ባልሆነ የመጀመሪያ ችሎት ከተማሪው ጋር መወያየት አለበት።

**1 ቀን**

**የተጻፈ ማሳወቂያ**

- የተጣሰው ደንብ ምንድነው
- የባህሪ ጥሰት ማስረጃ
- ምን ዓይነት የቅጣት እርምጃ እየተወሰደ ነው

ደግሞም ተማሪው ማብራሪያ እንዲሰጥ እድል መስጠት አለባቸው።

**ደረጃ 2**

**የመገለጫ ውሳኔ ስብሰባ (MDM)**

በተከታታይ ወይም በድምር በ1 አመት ውስጥ ወይም ተማሪው በተከታታይ በመወገድ ከተጠየቀ፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪው ለ10 ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ቀናት የሚቆይ መታገድ ወይም መባረር ማሳወቂያ ይደርሰዋል ።

ዲስትሪክቱ MDMን ከወላጆች፣ ከዲስትሪክት እና ከIEP ቡድን አባላት ጋር መሰብሰብ አለበት።

**10 ቀናት**

ዲስትሪክቱ የምደባ ለውጥ ከወሰነበት ቀን በኋላ MDM ከ10 የትምህርት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መከናወን አለበት።

እየተቀጣ ያለው ባህሪ ከአካል ጉዳታቸው ጋር የተያያዘ ነው

አዎ፣ እንደዛ ከሆነ ምንም የቅጣት እርምጃ አይኖርም፣ ተማሪው ከመታገዱ/ከመባረሩ አስቀድሞ ወደ ትምህርታዊ ምደባ መመለስ አለበት።

**ደረጃ 3**

የተግባራዊ ባህሪ ግምገማ መካሄድ እና የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ ማዘጋጀት አለበት።

አይ፣እንደዚያ ከሆነ መታገድ/መባረር ይቀጥላል።

**ደረጃ 3**

የተግባራዊ ባህሪ ግምገማ መካሄድ እና የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ ማዘጋጀት አለበት።

(!) ደግሞም ተማሪው በሚወገድበት ጊዜ ትምህርታዊ አገልግሎቶችን* መቀበል አለበት።

የተግባራዊ ባህሪ ግምገማ (FBA) እና የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ (BIP):- FBA የተማሪውን ባህሪ ተግባር ለመረዳት የሚያገለግል የግምገማ መሳሪያ ሲሆን አወንታዊ የጣልቃ ገብነት ድጋፎችን ለማዘጋጀት መሰረት ነው። ይህ ግምገማ ከታገደ እና ከተባረረ በኋላ ለ10 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት መከናወን አለበት (ተከታታይ ወይም ድምር)። FBA ያለውን BIP ለማዘመን ወይም አዲስ እቅድ ለማውጣት ይጠቅማል።

# ግብዐቶች፡-

ይህ የአጋዥ ግብዐቶች ዝርዝር ነው።

## የመንግስት ድርጅቶች፡-

**OSPI/የህዝብ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ፡-** https://www.k12.wa.us/student-success/special-education

**OEO/የትምህርት እንባ ጠባቂ ተቋም፡-** https://www.oeo.wa.gov/en

## የማህበረሰብ ድርጅቶች፡-

**የዲስሌክሲያ ዋሽንግተን ተርጓሚ፡-** https://www.facebook.com/decodingdyslexia.wa/

**የዋሽንግተን የአካል ጉዳት መብቶች፡-** https://www.disabilityrightswa.org/

**የፑጌት ሳውንድ የማህበረሰብ በሽታ ምልክቶች፡-** https://dscpugetsound.org/

**የዲስሌክሲያ አለማቀፍ ማህበር - WA ቅርንጫፍ፡-** https://www.wabida.org/

**በተማሪ አቅም ላይ መስራት፡-** https://studentpotential.org/

**የብዙባህል ቤተሰቦች የነጻነት ማዕከል፡-** https://www.multiculturalfamilies.org/

**በመብት ላይ የተመሰረተ፡-** https://rootedinrights.org/

**የማካተት መነሻዎች፡-** https://www.rootsofinclusion.org/

**የደቡብ ንጉስ ካውንቲ የቅጣት ህብረት፡-** https://www.skcdisciplinecoalition.com/

**የደቡብ ምስራቅ ሲያትል የትምህርት ህብረት** http://www.sesecwa.org/

**የኪንግ ካውንቲ አርክ፡-** https://arcofkingcounty.org/

**የዋሽንግተን ኦቲዝም እና የጥብቅና ስምምነት፡-** https://washingtonautismalliance.org/

**እጆች እና ድምጽ፡-** https://wahandsandvoices.org/

**የዋሽንግተን የብዙ ባህል አገልግሎቶች አገናኝ፡-** https://www.wmslink.org/

**አካል ጉዳተኞች፣ እድሎች፣ የበይነመረብ ስራ እና ቴክኖሎጂ (DO-IT)፡-** https://www.washington.edu/doit

**የሰሜን ምዕራብ የፍትህ ፕሮጀክት፡-** https://nwjustice.org/get-legal-help

**የቡድን ልጅ፡-** https://teamchild.org/

## ዘር እና የአካል ጉዳት፡-

**የአፍሪካ አሜሪካዊያን የድጋፍ ቡድን፣ የኪንግ ካውንቲ አርክ፡-** https://arcofkingcounty.org/community-calendar.html/event/2022/01/31/1643666400/african-american-support-group/361823

**የጥቁር ኦቲዝም፡-** https://www.autisminblack.org/about/

**የሲያትል የቀለም ቤተሰቦች፡-** https://www.focseattle.org/

**Kienan Ellis ትምህርታዊ ፕሮጀክት (KEEP)፡-** https://www.keep-wa.org/

**የዘር እና የአካል ጉዳት መሳበሪያ፡-** በመላው ሀገር ካሉ ወላጆች ጋር የሚደረጉ ውይይቶች፡- https://adayinourshoes.com/the-intersection-of-race-and-disabilities-conversations-with-parents-across-the-nation/

## የባህሪ ጤና አቅራቢዎች፡-

**የእስያ የምክር እና ሪፈራል አገልግሎት፡-** https://acrs.org/

**የአትላንቲክ ጎዳና ማእከል፡-** https://atlanticstreetcenter.org/

**Consejo ማማከር እና ሪፈራል፡-** https://consejocounseling.org/

**Cowlitz የሲያትል የጎሳ ጤና፡-** https://www.cowlitz.org/services/health-and-human-services/health-human-services-seattle.html

**Ingersoll የሥርዓተ-ፆታ ማዕከል፡-** https://ingersollgendercenter.org/

**የሲያትል የሙስሊም የጤና ባለሙያዎች፡-** http://www.mhpseattle.org/

**የሲያትል NAMI (ብሔራዊ የአእምሮ ሕመም ስምምነት)፡-** https://namiseattle.org/

**Naves፡-** https://www.navos.org/

**Ryther፡-** https://www.ryther.org/

**አንቺ ያደግሽ ሴት ልጅ!፡-** https://www.yougrowgirl.org/


**የልዩ ትምህርት የምህጻረ ቃሎች አገናኝ፡-** https://www.parentcenterhub.org/acronyms/

# የአካል ጉዳት ታሪክ እና ግንዛቤ

ከአካል ጉዳተኞች ማህበረሰብ የተገኙ አስተዋጾዎችን እና ታሪኮችን የሚያጎላ ይዘት




የንባብ ክፍል
https://seattlespecialeducationptsa.org/resources-for-families




የንባብ ክፍል / ታዳጊዎች እና ጎልማሶች
https://seattlespecialeducationptsa.org/resources-for-families

# ምንጮች

## ይህንን ሰነድ ለማዘጋጀት ከተጠቀሱትን ምንጮች አገናኞች

https://www.k12.wa.us/student-success/special-education

https://www.oeo.wa.gov/en

https://adayinourshoes.com/

https://www.seattleschools.org/

https://apps.leg.wa.gov/wac/default.aspx?cite=392-172a

https://www.parentcenterhub.org/

https://www.k12.wa.us/sites/default/files/public/specialed/pubdocs/ProceduralSafeguards.pdf

https://www.ada.gov/

https://www.seattleschools.org/about/school-board/policies/4200sp-a-visitors-to-schools/

### የቅጣት ምንጮች

[1] https://livesinthebalance.org/educators-schools/

[2] https://www.seattleschools.org/wp-content/uploads/2021/09/ADA-Discipline-Matrix-21-22.pdf

[3] https://www.seattleschools.org/wp-content/uploads/2021/11/SSR-21-22-november-2021.pdf

[4] https://www.understood.org/articles/en/functional-assessment-what-it-is-and-how-it-works

[5] https://www.understood.org/articles/en/behavior-intervention-plans-what-you-need-to-know

[6] https://www.wrightslaw.com/info/discipl.mdr.strategy.htm

[7] https://traumasensitiveschools.org

[8] https://www.nwjusticeforum.com

[9] https://livesinthebalance.org/our-solution/

[10] https://www.k12.wa.us/sites/default/files/public/2020%20Behavior%20Menu%20with%20ADA.pdf

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቀረበው ማስተኛ ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የታሰበ ነው። እንደ ሙያዊ ምክር የታሰበ አይደለም እና እንደዚያ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። የሲያትል ልዩ ትምህርት PTSA የተባለውን ጽሑፍ በመለጠፍ ህጋዊም ሆነ ሌላ የሙያዊ አገልግሎቶች ምላሽ ለመስጠት አልተሳተፈም። ህጋዊ ወይም ሌላ የተለየ የባለሙያ እርዳታ ካስፈለገ ሙያዊ አገልግሎት መፈለግ አለበት።

Seattle Special Education PTSA

# አባልነት

## ይቀላቀሉን እና ለውጥ ይፍጠሩ

# Seattle Special Education **PTSA**

## Informing, Educating, Empowering Communities

The Seattle Special Education PTSA advocates for all students with disabilitiesin the Seattle Public Schools District by:

- Helping families navigate the educational system
- Partnering with parents and educators to advocate for improvements in special education service delivery
- Providing educational resources to our members

**We hope you will join our advocacy community!**

For your convenience, there are multiple ways to join:

- Online: https://seattlespecialeducationptsa.org
- Mail: Seattle Special Ed PTSA, 7323 17th Ave NW, Seattle, WA 98117
- In person: Hand directly to a board member

We offer all memberships on a sliding scale, starting at no cost, going up by $5.00 increments. As of July 2021, the total cost that SSEPTSA pays per member is $12.26:

*Seattle Council PTSA dues = $3.50*
*Washington State and National PTSA dues = $8.00*
*Paypal fee = $0.76*
*Total = $12.26*

We encourage each individual to determine what contribution feels right and accessible to you.

Become a member! I'd like to contribute $ ____________

Name(s): ____________________

School affiliation: ____________________

Street Address: ____________________

City: ____________________ Zip Code: ____________________

Phone: ____________________ Email: ____________________

This email address may be used to offer electronic voting option, initial here to opt-out ____________

NOTE: PTA membership is NOT a commitment of your time! Becoming a member shows your support for the PTSA and helps fund advocacy efforts for all students with disabilities. Looking to do more? We always welcome greater involvement. Attend our monthly meetings and/or check one or more boxes below to find out more about our new committees.

- ☐ **Fundraising, Budget/Finance**
- ☐ **Racial Equity and Inclusion**
- ☐ **Family and Community Engagement (FACE)**
- ☐ **Membership**
- ☐ **Restraint and Isolation**
- ☐ **Inclusionary Practices**
- ☐ **Communications/Outreach**
- ☐ **Dyslexia**

For additional info, visit us at https://seattlespecialeducationptsa.org or follow us on Facebook ("Seattle Special Education PTSA")

https://seattlespecialedptsa.memberplanet.com/Membership.html

የአባልነት ቅጹ አገናኙ በ
**ክፍያ አማራጮች** ክፍል ስር ነው።